# Learning by Ear 2013

## መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE TEN: የሁለት ወንድማማቾች ወግ

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ካሳሁን TALKS TO አቶ ሙላቱ SISTER ወይዘሮ ለምለም**

- **ካሳሁን (M, 45)**
- **ወይዘሮ ለምለም (M, 40)**

**SCENE 2: ንጉሴ TRIES TO BEFRIEND ዳንኤል IN THE SCHOOLYARD**

- **ንጉሴ (M, 16)**
- **ዳንኤል (M, 16)**

**SCENE 3: ሉሊት TALKS TO ምህረት ABOUT HER TWIN BROTHERS KADU AND BANDA**

- **ሉሊት (F, 40)**
- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE 4: ወይዘሮ ለምለም TEXTS አቶ ሙላቱ AT A BAR**

- **አቶ ሙላቱ (F, 45)**
- **ወይዘሮ ለምለም (F, 40)**

1. **INTRO - NARRATOR:**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ትምህርታዊ ድራማ ክፍል አስር ነዉ። ባለፉት የድራማው ክፍሎች እንደተከታተልነዉ በቅርብ ጊዜዝያት በዳንኤል፣ በንጉሴ እና በምህረት ህይወት ውስጥ ብዙ ነገር ተከስቶአል። ዛሬ ወደምናቀርበዉ "የሁለት ወንድማማቾች ወግ" ወደተሰኘው ጭዉዉት ከመዝለቃችን በፊት ቀደም ሲል የተከሰቱትን ነገሮች ጠቅለል አድርገን እናስታውስ፡፡

ከአኅራባች ሀገር በመጣው አዲሱ ተማሪ ዳንኤል እና በክፍል አለቃዉ ንጉሴ መካከል የተፈጠረው ፉክክር አይሎ ሁለቱ ልጆች ትምህርት ቤት ውስጥ መደባደብ ሲጀምሩ ነገሩ ሁሉ ተጋግሎአል።

:

2. ንጉሴ (EP 08, 57): " ይበቃሃል፣ ዳንኤል! የአንተን ደደብ አስተያየቶች መስማትና እና መጥፎ ባህሪ ማየት በቅቶኛል,,,,, አሁን እንደ ወንድ እዚሁ ይዋጣልናል!"

3. ዳንኤል (LINE 60): "" ቀጥል! ይቺን እድል እየጠበቅሁ ነበር፡"."

ሁለቱ ወንዶች ምህረትን ለማግኘት ጥረት ላይ ናቸዉ ፤ ይህ ደግሞ ከዳንኤል ጋር ፍቅር የያዛት የልብ ጓደኛዋ ትዕግስትን አበሳጭቶአታል፡፡ ስለዚህ ትዕግስት በምስጢር ንጉሴ እና ምህረትን ለማገናኘት ማድባት ጀምራለች፡፡

4. ትዕግስት (EP 09, 60): " አንተም እንዳልከው እኔ ዳንኤልኤልኤልን ፈልጌዋለሁ፡፡ ስለዚህ እርሱን እንድቀርበው ከረዳኸኝ አንተን ደግሞ ከምህረት ጋር አቀራርብሀለሁ "

5. ንጉሴ: " ህምምም፤ ያዉ እንደምታውቂው ዳንኤልኤልኤል እና እኔ የልብ ጓደኞች አይደለንም… እንዴት ይረዳኛል ብለሽ ታስቢያለሽ?"

6. ትዕግስት: " ቀላል ነው! እንደ ምንም ብለህ ጓደኛ አድርገዋ፡፡"

ግን የትዕግስት ዕቅድ መስራት አለመስራቱን ከማየታችን በፊት ዳንኤል ወደመጣበት ላቦሪያ ወደተሰኘው አገር ተጉዘን ጉብኝት እናድርጋለን፡፡ አባቱ አቶ ካሳሁን ከቆንጆ ሴት ጋር ሻይ ቤት ተቀምጠል፡፡ ግን …ቆይ እስኪ! ግን ሴትዮዋ ወይዘሮ ለምለም፣ የምህረት አክስት …አይደለችም እንዴ?

## SCENE 1: ካሳሁን TALKS TO አቶ ሙሉቱ SISTER ወይዘሮ ለምለም

7. **SFX: CAFE AMBIENCE**

8. **ወይዘሮ ለምለም:** (romantic) አቶ፣ ካሳሁን፤ ስላገኘሁህ ደስ ብሎኛል! ለረጅም ጊዜ አላየሁህም! አንተም እንደእኔ ናፍቀኸኛል?

9. **ካሳሁን:** (nervous) ለምለም እባክሽን እስኪ አቁሚ ፡፡ አንቺ አይገባሽም! ትልቅ ችግር ገጥሞናል፡፡ ከኪሲምባ ያመጣሽልኝ ሁለቱ ሰራተኞች ልጆች ጠፍተዋል፡፡.

10. **ወይዘሮ ለምለም:** (shocked) ምን? ካሳሁን፣ ያ እንዴት ሊሆን ይችላል? ባንተ የማዕድን ማዉጫ ስፍራ ባንተዉ ቁጥጥርህ ስር ነበሩ! ይሀ እንዴት የእኔ ችግር ይሆናል?

11. **SFX: COFFEE CUP PUT DOWN ON SAUCER**

12. **ካሳሁን:** ለምለም ይችን ማምታታትሽን ወደ እኔ አታምጫት፡፡ ሰራተኞቹን ያመጣሽልኝ አንቺ ነሽ፤ እነሱ ደግሞ አሁን ድራሻቸውን አጥፍተዋል፡፡ ስለዚህ የገባሽበት ገብተሽ ፈልገሽ ማምጣት ይኖርብሻል፡፡

13. **ወይዘሮ ለምለም:** ግን እሺ አሁን እንዴት ላድርግ? አንዴ ካመጣሁልህ በኋላ ሀላፊነቱ የአንተ እንደሚሆን ተስማምተን ነበር። ከአንተ ያገኘሁት ገንዘብም ቢሆን፤ እነርሱ ሰርተዉ የሚያገኙት ነው። ስምምነታችን ያ ነበር።

14. **ካሳሁን:** ልክ ነው፣ ምን እንደተስማማን አውቃለሁ። ግን እንዲህ አይነቱ ነገር ሲያጋጥመን ይህ ለመጀመሪያ ግዜ ነው። ስታመጣሻቸው በደንብ ጠንቅቀሽ የምታውቂያቸው እስከሆነ ድረስ አሁን ፈልጎ ለማግኘቱትክክለኛው ሰው አንቺ ነሽ። ለልጆቹ ዝቅተኛ ግምት መስጠታችን የእኛ ስህተት ነው።ማስፈራራታችን ብቻውን ልጆቹ እንዳይጠፉ ዋስትና ነበር ብለን መጃጃላችን ስህተት ነበር፤ ያ በቂ የሆነ አይመስልም።

15. **ወይዘሮ ለምለም:** ካሳሁን እነዚያ ልጆች የመጡት በዓለም እጅግ ጎስቋላ ከሆነው መንደር ነው። ድሮም ቢሆን ስቃይ ይበዛባቸዋል፥ለመኖር የሚታገሉ ናቸው። ገንዘብ ለማምጣት ጎዳና ወጥተው እንዲለምኑ አባታቸው ይልካቸው እንደነበርና በወር ከሚያገኘው በላይም ይዘውለት እቤት ይገቡእንደነበር ነግሬህለሁ!

16. **ካሳሁን:** አንቺ ደግሞ ልክ እኮ ጀብደኞች ነው ያደረግሻቸው! ስሚ-የሆነ ሰው እጅ ከመግባታቸው በፊት ላገኛቸው እፈልጋለሁ! በተለይ ፖሊስ እጅ፥ ፥ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ።

17. **ወይዘሮ ለምለም:** አውቃለሁ! ካሳሁን፣ በደንብ አውቃለሁ፡፡ አትጨነቅ- እናገኛቸዋለን፡፡ ምንአልባት በመንገድ በኩል ብልሆች ሊሆኑ ቢችሉም ከላቦሪያ ወደ ካሲምባ ድንበሩን ተሻግረው ቤታቸው የሚደርሱ አይመስለኝም፡፡ አገኛቸዋለሁ፡፡

18. **ካሳሁን:** ለምለም፣ ብታገኛቸው ይሻላል፡፡ ደግሞ ውሎ ካደረ መዘዙ የከፋ ነው፡፡

19. **SFX: COFFEE BEING SIPPED**

20. **ወይዘሮ ለምለም:** እና እሺ አሁን ወርሃዊ ክፍያዎቹስ ?

21. **ካሳሁን:** ምን አልሽ ለምለም? ስራ ቦታ ላልተገኙ ሰራተኞች እንዴት እንድከፍልሽ ትጠብቂያለሽ? መጀመሪያ አግኚያቸው እና ስታገኚያቸው በቀጥታ እኔ ጋር አምጫቸው፡፡ በማዕድን ስፍራው ምን እየተካሄደ እንዳለ ለማንም አለመንገራቸውን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ፡፡.

22. **SFX: MOBILE PHONE RINGS**

23. **ካሳሁን: (picks up call)** ይቅርታ ይህን ስልክ ማንሳት አለብኝ፡፡-አቤት? ካሳሁን ነኝ……

24. **MUSIC INTERLUDE**

## SCENE 2: ንጉሴ TRIES TO BEFRIEND ዳንኤል IN THE SCHOOLYARD

**25. SCHOOLYARD ATMO**

**26. ንጉሴ:** ሃይ፣ ዳንኤል። እንዴት ነህ?

**27. ዳንኤል:** አይመለከትህም!

**28. ንጉሴ:** ስማ ሰውዬው። በመካከላችን ስላለው ጥላቻ በደንብ አሰብኩበትና ማቆም እንዳለብን ገባኝ። የሰላም ስምምነት ማድረግ አለብን።

**KW BEGIN**

**29. ዳንኤል:** (sceptical) ኧረ ባክህ፤ ተው እንጂ! እውነትህን ነው፣ ንጉሴ? መቼ እንድናደርገው ወሰንክ?

**30. ንጉሴ:** መቼ? ለጥቂት ቀናት ሳስብበት ቆይቻለሁ። አየህ ሁለታችንም አንድ ክፍል ውስጥ ነን። ብዙ ጊዜ አብረን አሳልፈናል። እርስ በእርሳችን አብረን መሆን ሊጠቅመን ይችላል።

**31. ዳንኤል:** ከአንተ ጋር መሆን ባልፈልግስ? ካየሁህ እለት ጀምሮ አልተመቸኸኝም።

**32. ንጉሴ:** እኔም እንደዛ፤ ግን የሰላም ድርድር እያቀረብኩ ነኝ። የመጣኸው ከሌላ ቦታ በመሆኑ እዚህ ጠላት ማፍራት ያለብህ አይመስለኝም። አየህ ህይወት ቀለል የሚልልህም-

**33. ዳንኤል:** (laughs sarcastically) ሃሃሃ። ምን አሰብክልኝ ባክህ ደህንነቴን የሚጠብቅ የጡት አባት ምናምን ያስፈልገኛል አይደል? ስማ ንጉሴ ማን እንደሆንኩ፣ ከየት እንደመጣሁ፣ ምን አይነት አቅም እንዳለኝ ምንም የምታውቀው ነገር የለም።

34. ንጉሴ: እኔም እንደዛ ማለት እችል ነበር። ግን ነገሩን ተወውና እጅ ለእጅ እንጨባበጥ ጓደኞችም መሆን፣ እንችላለን አይደል? ወይም ቢያንስ ጓደኛ ለመሆን እንሞክር።

**KW END**

35. ዳንኤል: (thoughtful) አይሆንም! አላምንህም። የሆነ አንዳች ተንኮል ቀምረክልኛል። እዚህ ላይ የሆነ ነገር እየፈለክ እንደሆነ ልነግርህ እችላለሁ...አይሆንም፣ ንጉሴ፣ ጓደኛ ልንሆን አንችልም። ግን ጠላት መሆንም አይገባንም። ይህ ስለ ምህረት ከሆነ ምህረት ስለእራሷ እንድትወስን እንተዋት። ቀላሉ ነገር ያ ነው።

36. ንጉሴ: (changes tone) አንተ ገገማ ገልቱ! እዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ህይወትህን አመሳቅዬው የመከራ ባላደርግልህ ቆይ ጠብቀኝ! ምነው እግሬን በሰበረው ባልመጣሁ ብለህ ትጸጸታታለህ!

37. ዳንኤል: (claps) ይኸው አሁን እስስቱ እውነተኛ ቀለሙ ገለጠ። ንጉሴ፣ በምንም ነገር አታሸንፈኝም! በትምህርት፣ በጸብ፣ ምህረትን በመውሰድ!

38. ንጉሴ: (angry) ገንዘብ በመስጠት የምታገኛት ከመሰለህ ደግመህ አስብበት! ምህረት የእኔ ናት! የመጣችው ከኪሲምባ ነው። ከየትም ከመጣ በተለይም ከላቦሪያ ከመጣ ጋር ፍቅር አይዛትም፡ የመጣህበት ቦታ ሂደህ ሴት ብትፈልግ ይሻልሀል!

39. **ዳንኤል:** (laughs) አቤት አቤት! ስለ ትንሿ ስጦታዬም አውቀሀልሳ? ማን ነገረህ ባክህ? ትዕግስት ናት?

40. **ንጉሴ:** ስማ ገንዘብ አንተ ጋር ብቻ ያለ እንዳይመስልህ፣ ዳንኤል! ይልቅ የማስጠነቅቅህ ከአሁን በኋላ እዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚኖርህ ቆይታ የከፋ እንደሚሆን ነው። በፍጥነት እቃዎችህን ሸክፈህ የሚቀጥለውን አውቶቡስ በመያዝ ፣ ወይንም በአውሮፕላን ተሳፍረህ፣ ብቻ የፈለገው ይሁንወደ አዛ ወደ መጣህበት ላቦሪያ የሚያደርስህን ብታመቻች ነው የሚበጅህ፡፡ የምናገረዉ ይግባህ! ጠብቅ!!

41. **MUSIC INTERLUDE**

## <u>SCENE 3: ሉሊት TALKS TO ምህረት ABOUT HER TWIN BROTHERS KADU AND BANDA</u>

42. **ATMO: ምህረት NEW HOME, AT NIGHT**

43. **SFX: PAGES OF A BOOK BEING TURNED**

44. **SFX: QUIET FOOTSTEPS**

45. **ሉሊት:** ምህረት፣ አሁንም እያጠናሽ ነው??

46. **ምህረት:** አዎ፣ ግን እየጨረኩ ነው፡፡ በቅርቡ የመጀመሪያዎቹን ፈተናዎቻች እንፈተናለን፡፡.

47. **ሉሊት:** ምህረት፣ መተኛት አልቻልኩም፡፡ ብዙ ነገር ተፈፅሞአል፡፡ እንደዉ እያበድኩ እንደሆን ነዉ የሚሰማኝ፡፡

48. ምህረት: ስለዚህ ጉዳይ ከአባቴ ጋር መነጋገር አልነበረብሽም? ምንአልባት ከዶክተርሩ ጋር፣?

49. ሉሊት: አይሆንም፣ አባትሽ እዚህ የለም፤ ታውቂዋለሽ። ወደ ቤት የሚመጣው አኩለሌሊት ላይ እንዲያ በመጠጥ ጥምብዝ ብሎ ነው። ምን እየተናገርኩ እንደሆነ መረዳቱን ተይውና ያልኩትን በቅጡ መስማቱንም እንጃ።

50. ምህረት: ይቅትታ እማዬ እንዴት ልረዳሽ እንደምችል አላውቅም።.

51. ሉሊት: (concerned) ምህረት፣ ሁለት ታናናሽ ወንድሞችሽ አልናፈቁሽም? ስለ እነርሱ እንዴት አትናገሪም? መኖራቸውን እንኳ የረሳሻቸው ትምስያለሽ።

52. ምህረት: ኸረ እማዬ እንዴ! እየተናገርኩ እኮ ነው! ግን ስለ እነርሱ ሳነሳ ሁል ጊዜም አባዬ ችላ ነው የሚለኝ! እኔም እየተገረምኩ አይ በቃ አሁን ከአክስቴ ወይዘሮ ለምለም ጋር በመሆናቸው የተሻለ ኑሮ እየኖሩ ነው ብሎ ስላሰበ ይሆናል እላለሁ። እና ግን እማ በዚህ ሀሳብ ከአባቴ ጋር አልተስማማሽም ነበር?

53. ሉሊት: (sorrowful) አዎ-አልተስማማሁም ምን አማራጭ ነበረኝ ታዲያ። ኑሮዋችን ከእጅ ወደ አፍ ስለነበር ለሁላችሁም የሚበቃ መውደቂያም አልነበረን። እያደጋችሁ ከመጣችሁ በኋላ ደግሞ አንቺ ከእነሱ ጋር አንድ አልጋ ተጋርተሽ መተኛት አትችይም።

54. ምህረት: አሃ,,,, ገባኝ፣

**55.** **ሉሊት:** (bitterly) ግን ቢያንስ አንድ ቤተሰብ ነበርን። እንዲኖረኝ እመኘው የነበረውን ነገር ያሟላ የሚመስል አዲስ ቤት አሁን ቢኖረንም ሀዘን ይሰማኛል። ከበፊቱ አሁን ይከፋኛል።

**56.** **ምህረት**: ግድ የለም ታልፊዋለሽ። እኔም እየሞከርኩ ያለሁት ይህንኑ ነው። ግን አንድ ነገር እማዬ አባዬ አዲስ ስራ አግኝቷል? ማለቴ ከጥቂት ቀናት በፊት የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ እንኳ መግዛት አልቻልንም ነበር። ሁለታችሁ ከጥሎሽ ለምታገኙት ስትሉ ልትድሩኝ ስታስቡም ነበር። አሁን በድንገት በዚህ አዲስ ቤት እየኖርን ነው፤ በእዚያላይቴሌቪዥን እንኳ አለን!

**57.** **ሉሊት:** የእኔ ልጅ፣ ምህረት አባትሽን በተመለከተ ልክ እንዳንቺው እኔንም ግራ ገብቶኛል። ልል የምችለው ነገር ባገኘነው እየተደሰትን በዚሁ እንዲዘልቅ ተስፋ ማድረግ ነው፡

**58.** **MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 4:</u> ወይዘሮ ለምለም <u>TEXTS</u> አቶ ሙላቱ <u>AT A BAR</u>**

**59.** **BAR ATMO AT NIGHT**

**60.** **SFX: MESSAGE RINGTONE FOR INCOMING SMS**

**61.** **አቶ ሙላቱ :** (drunk voice) በእዚህ ምሽት ደግሞ በስልኬ መልዕክት የሚልክልኝ ማን ነው? አንዳንድ ሰዎች መሸ አልመሸ ስለ ጊዜ ስሜት የላቸውም። ይቅርታ፣ ጓዶቼ፣ አሁን እመለሳለሁ፡

**62.** **SFX: CHAIR BEING DRAGGED SLIGHTLY**

**63. SFX: PHONE BEEPING AS WHEN TEXT IS READ**

**64. አቶ ሙላቱ :** እንዴ? ለምለም? እህቴ ደግሞ ከእኔ ምን ፈለገች? እስኪ እንየዉ.... **(reads text)** "ሃይ ሙላቱ፤ ልጆችህ መጥፋታቸውን እወቅ፡፡ ግን አትጨነቅ፡፡ እንዲመለሱ ለማድረግ የቻልኩትን ሁሉ አደርጋለሁ፡፡ ከሰላምታ ጋር፡፡ ለምለም""

**65. አቶ ሙላቱ :** **(drunk voice)** በጭራሽ አይ...ይሄ እውነት አይደለም፡፡ አላምንም፡፡ እንዲናትና፤ ቆይ ልደውልና የምትለውን ልስማ!

**66. SFX: PHONE BEING DIALLED**

**67. ወይዘሮ ለምለም:** **(on the phone, sleepy tone)** ምምም...ሃሎ፣ ለምለም ,

**68. አቶ ሙላቱ :** **(drunk: jokingly, on the phone)** ለምለም፣ መልዕክትሽ ደርሶኛል! ምን ማለትሽ ነው? ልጆችህ ጠፉ ስትዪ? እየቀለድሽ መሆን አለበት! ሉሊትን ለመጉዳት ብለሽው ነው? ሚስቴ ምን አደረገችሽ? በነገራችን ላይ ጥቂት ገንዘብ እፈልጋለሁ፡፡ እንደውም ከአንቺ ገንዘብ ካገኘሁሰነባብቷል፡፡

**69. ወይዘሮ ለምለም:** **(concerned)** ወይ ጉድ፣ ሙላቱ፣ የኔ ወንድም፣ ለምንድን ነው ግን እንደ ቁም ነገረኛ የማትቆጥረኝ...

**70. MUSIC INTERLUDE**

## 71. OUTRO - NARRATOR

በዚህ በአቶ ሙላቱ  እና በእህታቸው መካከል በነበረው የስልክ ውይይት መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ የተሰኘዉን ከዶይቸ ቬለ የሚተላለፈዉን ተከታታይ ትምህርታዊ ድራማ  አስረኛ ክፍል እናጠናቅቃለን፡፡ ወሮ ሉሊት ስለ ሁለቱ  ልጆች መጥፋት ሲሰሙ ምን ያደርጉ ይሆን? ንጉሴ ከዳንኤል  ጋር የፈለገው ጓደኝነት ካልተሳካ ምን ይዶልትበት ይሆን? የእነዚህን መልሶች በሚቀጥለዉ ክፍል ድራማ ይከታተሉ። ያለፉትን ድራማ ክፍሎች ማድመጥ ከፈለጉ አልያም ድራማዉን በግል ማህደሮ ውስጥ መገልበጥ ከፈለጉ የድረ-ገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ ያገኙታል። በፋፌስቡክ አድራሻችንም ዝግጅቶቻችን መከታተል ትችላላችሁ። በሚቀጥለዉ ክፍል ድራማ እስክንገኛኝ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።